**በእኔና በጥቂቶች ሃላፊነትና ተሳትፎ የተሰበሰበውን የህዝብ ገንዘብ በተመለከት።**

**<u>ለብፁዕ አእቡነ ቴዎፍሎስ</u>**
**<u>እና</u>**
**<u>ለአማራ ፋኖ ህዝባዊ ሠራዊት አመራር:</u>**

**<u>አንደኛ:-</u>**

በአማራ ህዝብ፡ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እና በምዕመናኑ ላይ በመካሄድ ላይ ያለውን የዘር ፍጅትና ሌሎችም ወንጀሎችን በተመለከተ ለዓለም አቀፉ ፍርድ ቤት እንዲቀርብ ጥረት ለማድረግ አንድ ኮሜቴ እንዲቋቋምና በዚህም ውስጥ እኔ እንድሳተፍ በብፁዕ አባታችን አቡነ ቴዎፍሎስ የቀረበልንን ጥያቄ ተቀብለን በእሳቸው ሊቀመንበርነት በተቋቋመው ( የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የዘር-ጥፋት መከላከያ ተቋም (ኢተክዘተ) ወይም Orthodox Tewahedo Church Against Genocide in Ethiopia (OTAGE) በተባለው ኮሚቴ ውስጥ የህግ ክፍል ሃላፊ ሆኜ ለሁለት አመት በነፃ ሰርቻለሁ:: በጊዜው ጉዳዩ ትልቅ አንገብጋቢ ጥያቄ ስለነበረ መደበኛ ስራዬን ሙሉ ለሙሉ ለቅቄ በዚያን ወቅት ከምኖርበት አፍሪካ መጥቼ ሌት ተቀን በስሜትና በጉጉት ሰርቻለሁ:: በዚህም ወቅት ለጉዞም ሆነ ለመቆያ ለእኔም ሆነ ለሌሎች የተከፈለ እና እኔም የጠየቅሁት ገንዘብ የለም::

መረጃ በማሰባሰብና ጉዳዩን ወደ ኢንተርናሽናል ፍርድ ቤት ( ICC) ለማቅረብ: ለእያንደንዱ ወንጀል የክስ ምስረታውን ማዘጋጀትና አጠናቅሮ በመጀመሪያ በዚህ መስክ ለተሰማሩ የህግ አዋቂዎች እንዲመለከቱት ማድረግ ብዙ ፈታኝ እና አድካሚ ስራ ሆኖብን ነበር:: ሕግን በተመለከተ የነበርን ባለሙያዎች ሁለት ሰዎች ብቻ ነበርን:: ከጥቂት ጊዜ በኋላም ባልደረባዬ በጊዜ ጥበት ለቆ ወጣ:: በሌሎች ዘርፎችም በበጎ ፈቃድ የተሰማሩ ብዙ ምሁራን ነበሩ::ለቀው ወጡ:: የቀረነው ጥቂት የቤተ ክህነቱ ሰዎችና ሌሎች ባለሙያዎች ነበርን::

OTAGE የቤተክህነቱ Global Outreach በአቡነ ቴዎፍሎስ የሚመራው ድርጅት ቅርንጫፍ ነው:: በዚሁ ድርጅት በጥንቃቄ ለOTAGE ስራ ተብሎ በስነ ስርአት እንዲውል ታስቦ በእኔ ግምባር ቀድምትነት በሚዲያ በተለይም በ360: በኢትዮጵያ ድምፅ: በቤተሰብ ሚዲያ ተሳትፎ ወደ አራት መቶ ሺህ ዶላር ተሰብስቦአል:: በዚህ ገንዘብ አሰባሰብ ትልቁን ሚና የተጫወትኩ እኔ በመሆኔ ሀላፊነቱ ይስማኛል:: ከዚህ ውስጥ የተወሰነ ገንዘብ ጄኔቭ ለሚገኝ የኢንተርናሽናል የህግ ኩባንያ ሲከፈል ከ390 ሺህ ዶላር በላይ በብፁዕ አባታችንና ሊቀመዘምራን ይልማ በሚያዙበት ( global outreach)/(ግሎባል አውትሪች) አካውንት ውስጥ ነበረ::: ይህ ገንዘብ የተሰበሰበበትን አላማ አስመልክቶ ወደፊት እንዳይራመድ በሃገራችን በተከሰተው ጦርነትና በተፈጠረው ምስቅልቅል ምክንያት የተሰራ ስራ ስለሌለ ይህ ገንዘብ በተባለው አካውንት ውስጥ እንደሚኖር አምናለሁ::

እኛ የጀመርነው ስራ ከአምስት አመት በፊት በአማራና በቤተክህነቱ ላይ በተፈፀመው የዘር ጭፍጨፋ መፈናቀሎችና የቤተ ክርስትያን ማቃጠል በምዕመናን ላይ በደረሰው ፍጅትና እልቂት ላይ ሲሆን ከዚያ በሁዋላ በአማራ ላይ ያነጣጠረው ጥቃት እየከፋ በመምጣቱና ቀጥሎም ወያኔ በከፈተው ጦርነት የተፈፀሙት የበለጠ ትኩረት ስላገኙ ይህ የእኛ ስራ ትኩረት ሊያገኝ አልቻለም:: በበኩሌ ከ ICC (International Criminal Court) ዋና ፕሮሲኩተርና በእሷ ስር ካሉ የህግ ባለሙያውች ጋር ቀጥታ ግንኙነት በመፍጠር ኢትዮጵያ የሮም ኢንተርናሽናል ስምምነት ( Rome Statute 2002) ፈራሚ አባል ባለመሆንዋ ጉዳዮችንን በቀጥታ ለICC ማቅረብ ስለማንችል የሌሎች መንግስታትን ድጋፍና ተባባሪነት በሚጠይቀው አሰራር ላይ ብዙ ተወያይተናል: ተፃፅፈናል:: በተለይም አንዱ አቋራጭ መንገድ የተባበሩት መንግስታት የሰብአዊ መብት ኮሚሽን የተጠናቀረውን ሪፓርት ወደ ተባበሩት መንግስታት የፀጥታ ምክር ቤት እንዲልክና ምክር ቤቱ በውሳኔ ወደ ኢንተርናሽናል ወንጀለኛ ፍርድ ቤት ( ICC) እንዲመራው ለማድረግ በቀረነው ጥቂት ስዎች ከባድ ጥረት ተድርጎአል::

በእኛ በኩል ከእምስት  አመት በፊት በሻሸመኔ: በመተከል ለተፈፀሙት ወንጀሎች ጥናቱን አጠናቀን ለኢንተርናሽናል የህግ እማካሪዎች የወንጀሎቹን አይነትና የተከሳሾችን ዝርዝር አቅርበናል:: የወለጋና የአጣዬንም በተመለከተ በእኛ በኩል ምርመራና ጥናት አጠናቀን አቅርበናል:: ፍርድ ቤቶች የሚፈልጉት ኦሪጅናል የፅሁፍ : የምስል የቪድዩ:  የምስክሮች: የጊዜ : የቦታና እንዲሁም ተከሳሾችን ከወንጀሎች ጋር የሚያያይዙ መረጃዎች ነው:: ይህንን ገንዘብ በማይከፈላቸው በፈቃደኛነት በሚሰሩ ወገኖቻችን በጥሩ ሁኔታ ተቀናብሮ  የህግ አማካሪዎች በሚጠይቁት ፎርማት  ውስጥ በማስገባት ከባድና የባለሙያዎች እውቀት ግዜና ብዙ ወጪ ሊያስወጣ የሚችል ዝግጅት በበጎፈቃደኞች ትሳትፎ ተሰርቶ ነበር::  ከዚያ በኋላ በጣም በከፋ መልኩ የተፈፀሙትን ብዙ ወንጀሎች ለማካተት ብዙ  ድካም ጠየቀን:: የሰው ሃይላችንም መነመነ:: የህግ አዋቂ እኔ ብቻ ቀረሁ:: በመረጃ አሰባስብ የተስማሩትም ስራው ስለተራዝመባቸው ተበተኑ::

ሊቀ መንበራችን ብፁዕ አቡነ ቴዎፍሎስ በማናውቀው  ምክንያት ሊሰብስቡን  አልቻሉም:: እሳቸውን ማግኘት ፈፅሞ አልተቻለም:: በማን ስም እንድምሰራም ማወቅ  አልቻልኩም::ሌሎችም አካባቢዬ የነበሩ በተለያየ ዘርፎች ለመቀጠል ዝግጁ የነበሩ በሊቀመንበሩ መጥፋት አዝነው ስራውን ለቀቁ:: እኔ በኤፕሪል 2022 ለሚመለከታቸው  በተለይ በጣም ብዙ እርዳታና ድጋፍ ለሰጠን የቤተስብ ሚዲያ አሳውቄ ከስራው ተሰናበትኩኝ:: ከስራ ጓደኞቼ ጋር ተመካክረን የተሰበሰቡትን መረጃዎች ሁሉ ከአማዞን repository ተከራይተን አስቀምጠናል:: ወደ አራት መቶ ሺህ ዶላር የሚጠጋ ገንዘብ ደግሞ በግሎባል አውት ሪች ልዩ አካውንት ውስጥ ይገኛል::

ዛሬ በግሎባል እውት ሪች አካውንት  ያለውን  ይህንን ገንዘብ የማንቀሳቀስ  ስልጣን ያላቸውን  ሊቀ መዘምራን ይልማን የምጠይቀው በእኔ ቀዳሚ ተሳትፎ የዘር ማጥፋትን ወንጀሎችን ለማስቆምና ወንጀለኞችን ለመቅጣት እንዲቻል የተሰበሰበው ገንዘብ በአሁኑ ጊዜ ለታለመለት አላማ  ለማዋል ጊዜው ስለ ማይፈቅድ የአማራን ሕዝብ ከሕልውና  መጥፋት ኢትዮጵያንም ከመፍረስ አደጋ ለመከላከል ተጋድሎ ላይ ላለው የአማራ  ህዝብ  በስብአዊ እርዳታ   እንዲስጥ  እንዲያደርጉ በአክብሮት እጠይቃለሁ::

**<u>ሁለተኛ</u>**

በአርበኛ እስክንድር ነጋ  ጥያቄ የአማራ ህዝባዊ ግንባር ድጋፍ ሰጪ ግብረ ሃይል ሊቀመንበር በነበኩበት ጊዜ ለፋኖ ትግል ማከናውኛ በገንዘብ ስብስባ ዋናውን ሚና   ተጫውቻለሁ::  በሊቀመንበርነት ባገለገልኩበት የስድስት ወር ጊዜ ውስጥ  ብዙ ገንዘብ ተሰብስቦል:: ከዚህ ውስጥ ወደ ስድስት መቶ ሺህ ዶላር የሚጠጋ ገንዘብ  እኔ በነበርኩበት ጊዜ አብዛኛው በእኔ ስልጣን ለፋኖ ከግንባሩ ጋር ለሚሰሩቱም ለማይሰሩትም  የተከፋፈለ ሲሆን ከዚህ ውጭ ከ 1.2 ሚሊዮን ዶላር በላይ በአካውንት  ውስጥ ነበር:: ከከባንክ ኦፍ አሜሪካ ውጭ ሌላም ባንክ ላይ ታግዶ ከነበረው ጋር ሲደመር ከ1.2 ሚሊዮን  ዶላር  በላይ በአካውንቱ ውስጥ አለ ብዬ እምናለሁ::

ይህ ገንዘብ የተገኘው በእኔ ሃላፊነትና በግብረ ሀይሉ አባላት ሙሉ ተሳትፎ በተካሄደ የቴሌቶን ገንዘብ ስብሰባ ዝግጅትና እኔ እራሴ በዋሽንግተን ዲሲ: በኮሎራዶ: በሚኒሶታ: ቴክሳስ: ካሊፎርኒያ: ቦስተን: ካልጋሪ: ኤድመንተን: ቶሮንቶ: ለንደን: በአካል በመሳተፍ እንዲሁም በዙምና በቴሌ ኮንፈረንስ በተደረገ የእርዳታ ስብስባ: የአማራ  ወንድሞቼና  እህቶቼ ፊት ተገኝቼ በመናገር እና በማስተባበር : ጥያቄዎችን ቀጥታ በመመለስ ያስገኘሁት ገንዘብ ነው:: ገንዘቡ የትሰብሰበው ላንድ ፋኖ አድረጃጀት ሳይሆን ለሁሉም ፋኖ እንደሚሰጥ በሕዝብ ፊት ቃል ገብቼ ያስገኘሁት  ስለሆነ ይህም ገንዘብ ከአካውንት ወጥቶ በአስችኳይ ለሁሉም ዕዞች  እንዲከፋፈል   አጥብቄ እጠይቅለሁ:: ይህ ገንዘብ መዳረሻው ፋኖ ነው:: ባንክ እካውንት አይደለም:: ለአንድ የተወሰነ ክፍልም አይእለም. ጸረ አማራው የአብይ አህመድ ሠው በላ ሠራዊት ያለ የሌለውን ሃይል አሟጦ የፉኖን ተጋድሎ ለመደምሰስ የመጨረሻ ያለውን ዘመቻ በከፈተብት በዚህ ወቅት፤ እንኳን ለፉኖ የተዋጣው፤ አይደለም ሁሉም አማራ ያለውን ሁሉ አሟጦ ፉኖን መርዳት ያለበት አጣዳፊ ሁኔታ ላይ መሆኑ ታውቆ ቀና ትብብር እንድታደርጉ በአርበኞቻችን ስም ጥሪዬን አቀርባለሁ::

**ማጠቃለያ**

በአሁኑ ወቅት ፋኖ ከመቼውም ጊዜ የበለጠ ድጋፍ የሚፈልግበት የትግል ምዕራፍ ላይ ነው::: ይህ ገንዘብ እዚህ የሚቀመጥበት ምንም ምክንያት የለም:: በበኩሌ የሰው ፊት ቀርቤ: ተሞግቼም: : ተጠይቄም: ተዘልፌም፤ ለፋኖ ብዬ ጮኬ ተማጥኜ ይህ እርዳታ ሊገኝ የተቻለው ህዝባችን እኔ በተናገርኩትና ቃል በገባሁት አደራ ላይ እምነት ስላለው ነው:: ይህን የተጣለብኝን አደራ ሳላሟላ ክንዴን አልንተራስም::ስለዚህም በኦቴጅ ስም የተውጣጣው በሊቀ መዘምራን ይልማ ቁጥጥር ስር ያለው ገንዘብና በግንባሩ አካውንት ውስጥ ያለው በድምሩ እንድ ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ዶላር ካሉበት አካውንት ወጥተው በአራቱም ክፍለሃገር የሚታገሉት ፋኖዎች ሊያዙበትና በእነሱ ውሳኔና ስምምነት ሊከፋፈሉ ወደ ሚችሉበት ሁኔታ በአስችኳይ እንዲተላለፍ እጠይቃለሁ:: የአራቱ ክፍለሃገር ፋኖዎች ፈቃድ ይፈፅማል:: የሚመለከታቸው ሁሉ ለዚህ ጥያቄ አፈፃፀም ግፊት እንዲያደርጉ በትግሉ ስም እጠይቃለሁ።የፋኖ አመራሮች ይህ ገንዘብ የሚተላለፍበትን እካውንትና ከውስብስብ ፓለቲካ ነፃ የሆነ ወኪል ቡድን ሲገልፁልን ህዝባችን በልዩ ዘመቻ እራት መቶ ሺህ ዶላር ጨምሮ ሁለት ሚሊዮን በመሙላት ፋኖአችንን ለወሳኙ ድል ማብቃት ይቻላል::

ድል ለሕዝባችን!!! ለወሳኙ ትግል ወደፊት!!! ሁሉ ነገር ወደ ፋኖ !!!ፋኖ ያቸንፋል

ዳዊት ወልደ ጊዮርጊስ June 17, 2024